# <u>የኢትዮጵያ የግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት የዘር፣ ሌሎች የምርምር ውጤቶች እና የተረፈ ምርት ሽያጭ አፈፃፀም መመሪያ ቁጥር …/ 2016</u>

ኢንስቲትዩቱ የባለድርሻ አካላት ፍለጎት ለማርካት ጥራትና ወቅቱን የጠበቀ እንዲሁም በዘመናዊ የቴክኖሎጂ ብዜት ስርዓት አምርቶ ለተጠቃሚዎች ማቅረብ ያስፈልጋል፡፡ ስለሆነም ኢንስቲትዩቱ የተቀላጠፈ የሽያጭ ሥርዓት በመጠቀም ተልዕኮውን ለመወጣት እንዲያስችለው በየማዕከሉ ከምርምር የሚገኙ የምርምር ምርቶችና ተረፈ ምርቶች ሲሸጡ በቂ ቁጥጥርና የአሰራር ሥርዓት መዘርጋት አስፈልጓል፤

ስለሆነም ለኢንስቲትዩቱ የዘር፣ ሌሎች የምርምር ውጤቶችና ተረፈ ምርት ሽያጭ ሂደት የሚመራበት አሰራር ተግባራዊ ማድረግ እንዲቻል፤ በሽያጭ ሥራዎች ውስጥ ሊተገበሩ የሚገባቸውን ዝርዝር መስፈርቶችን በማካተት በሽያጭ ሥራ ላይ የሚሳተፉ አካላት እንዲገለገሉበት፤ ወጥነት ያለው የባለድርሻ አካላት ዕርካታና ገፅታ መገንባት አስፈልጓል፤

በዚህ መነሻ የመንግሥት ህጎች፣ የሌሎች መሰል ተቋማትን የአፈፃፀም ልምድ በማገናዘብ፣ የባለድርሻዎችን ፍላጐት ከግንዛቤ ውስጥ በማስገባት እንዲሁም በንስቲትዩቱ ማቋቋሚያ ደንብ 527/2015 አንቀጽ 6(4) የተሰጠውን ተልዕኮ ለማሳካት ኃላፊነትና ተጠያቂነትን በየደረጃው በማስቀመጥ ይህ የኢትዮጵያ የግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት የዘር፣ ሌሎች የምርምር ውጤቶች እና የተረፈ ምርት ሽያጭ አፈፃፀም መመሪያ ነባሩን መመሪያ ቁጥር …… በማሻሻል ተዘጋጅቶ ቀርቧል፡፡

## 1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "የኢትዮጵያ የግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት የዘር፣ ሌሎች የምርምር ውጤቶች እና የተረፈ ምርት ሽያጭ አፈፃፀም መመሪያ ቁጥር …/ 2016" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

## 2. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፤

2.1 ግልፅ ጨረታ፡- ማለት የሽያጭ ማስታወቂያው ሰፊ ሽፋን እንዲያገኝ በሬዲዮ፣ በጋዜጣ ወይም በቴሌቪዥን የሚገለፅ ማለት ነው፡፡

2.2 ውስን ጨረታ፡- ማለት የሽያጭ ማስታወቂያ በደብዳቤ ተዘጋጅቶ ማህተም አርፎበት ለተመረጡ ድርጅቶች የሚሰራጭ ማለት ነው፡፡

2.3 የገበያ ጥናት፡ ማለት ለሚሸጠው ምርት ወደፊት ገበያው ምን ሊመስል እንደሚችል ስፋት ባለው አኳኋን ዋጋ የሚጠናበት ስልት ማለት ነው፡፡

2.4 የዋጋ ዳሰሳ፡ ማለት ሽያጩ በታሰበበት ወቅትና ምርቱ በሚፈለግበት አካባቢ ዋጋው ምን እንደሚመስል ዕለታዊ መረጃ የሚሰበሰብበት ሂደት ነው፡፡

2.5 የምርምር ቴክኖሎጂ፡- ማለት በማመንጨት፤ በማላመድ ወይም በሌላ የምርምር ሂደት የሚገኝ ህያው ወይም ህያው ያልሆነ የምርምር ውጤት፤ የቴክኒክ፣ የክህሎትና የአሠራር ዘዴ ነው፡፡

2.6 ዝርያ፡ ማለት በአንድ የዕፅዋት/እንስሳት ምድብ ውስጥ የታወቀ የመጨረሻ ዝቅተኛ ደረጃ ያለው ሆኖ ከአንድ ከተወሰነ ጄኖታይፐ ወይም ከብዙ ጄኖታይፖች ጥምረት በሚመነጩ ባህርያት በመታየት ራሱን የሚገለጽ፤ ካሉት ባህርያት መካከል ቢያንስ በአንዱ ከሌሎች ማናቸውም የዕፅዋት/የእንስሳት ምድብ የሚለይ እና ባህርያቱን ሳይቀይር መራባት በመቻሉ ምክንያት እንደ አንድ ዓይነት ምድብ ሊወሰድ የሚችል ነው፡፡

2.7 ሌሎች የምርምር ውጤቶች፡ ማለት ህያው ያልሆኑ የግብርና ምህንድስና ውጤቶች፤ የምርምር ፕሮቶኮሎችና ፓተንቶችን የሚያካትት ነው፡፡

2.8 ዘር፡ ማለት ለዕፅዋት/እንስሳት ማራባት የሚያገለግል እውን ዘር፣ የእንስሳት አባለዘር፤ ደቂቅ ዘአካላት፤ ቨርሚ ትል፤ አኩራች፣ የተክል ቁርጥራጭ፣ ሥራ ሥር፣ ችግኝ፣ ሳዮን፣ መሰረተ ግንድ ወይም ሌላ ዓይነት የተክል አካል ነው፡፡

2.9 መነሻ ዘር፡ ማለት የአንድን ዘር ደረጃ ለማምረት በምንጭነት የሚያገለግል ዘር ነው፡፡

2.10 የዘር ደረጃ፡ ማለት አራቢን፣ ቅድመ መስራችን እና መስራች ዘርን የሚያካትት ነው፡፡

2.11 አራቢ ዘር፡ ማለት የመጀመሪያ የዘር ደረጃ ነው፡፡

2.12 ቅድመ መስራች ዘር፡- ማለት ከአራቢ ዘር የሚገኝ የዘር ደረጃ ነው፡፡

2.13 መስራች ዘር፡ ማለት ከቅድመ መስራች ዘር የሚገኝ የዘር ደረጃ ነው፡፡

2.14 ተረፈ ምርት፡- ማለት ተቋሙ ለዘር ምርት ከሚያቀርበው ቴክኖሎጂ ውስጥ በተለያየ አሳማኝ ምክንያት ከዘር ሽያጭ የተረፈ ሆኖ ምርቱ ለምግብነት እና ለተለያየ አገልግሎት የሚውል ማለት ነው፡፡

2.15 የሽያጭ ኮሚቴ፡ ማለት የዘር፤ ሌሎች የምርምር ውጤቶችና ተረፈ ምርት ሽያጭ ለማስፈፀም የሚሰየም ኮሚቴ ማለት ነው፡፡

2.16 ማዕከላት፡- ማለት ተጠሪነታቸው ለኢትዮጵያ የግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት የሆኑ፤ በተለያየ ክልል የሚገኙና የተለያዩ ሰብሎች፤ የእንስሳት፤ የተፈጥሮ ሃብት እና የግብርና ሜካናይዜሽን ምርምር የሚካሄድባቸው ቦታዎች ናቸው፡፡

2.17 ተቋም፡- ማለት የኢትዮጵያ የግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት ነው፡፡

2.18 ዋና ዳይሬክተር፡- የኢትዮጵያ የግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት የበላይ ኃላፊ ማለት ነው፡፡

2.19 ዳይሬክተር፡- ተጠሪነታቸው ለተቋሙ ዋና ዳይሬክተር የሆኑ የዋና መስሪያ ቤት ወይም የማዕከል ኃላፊዎች ማለት ነው፡፡

3. **የተፈፃሚነት ወሰን** ይህ መመሪያ የኢትዮጵያ ግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት በሚያወጣቸው ዘር፤ ሌሎች የምርምር ውጤቶች እና ተረፈ ምርቶች ሽያጭ ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

4. **ዓላማ** ኢንስቲትዩቱ በምርምር የሚያወጣቸውን የዘር፤ የሌሎች የምርምር ውጤቶች እና ተረፈ ምርት ሽያጭ አፈፃፀም የተቋሙን የውስጥ ገቢ ለማሳደግ፣ ግልጽነትንና ተጠያቂነትን የተላበሰ፣ ቀልጣፋና ውጤታማ አሰራር በመዘርጋት በተገቢው ቦታ፣ ጊዜና ዓይነት ለተገልጋይ ተደራሽ እንዲሆን ለማድረግ ነው፡፡

## 5. የዘር፣ የሌሎች የምርምር ውጤቶች እና ተረፈ ምርቶች ሽያጭ ሂደት

### 5.1 የዘር፣ የሌሎች የምርምር ውጤቶች እና ተረፈ ምርትን አሰባሰብ

5.1.1 ማንኛውም የሥራ ዘርፍ በምርምር ያወጣውን ለሽያጭ የሚውል የዘር፣ የምርምር ውጤቶች እና ተረፈ ምርት ወቅቱን ጠብቆ ለመሰረታዊ አገልግሎቶች ሥራ አስፈፃሚ ማስረከብ አለበት፡፡ (የመረካከቢያ ቅፅ - 2 ተያይዟል)

5.1.2 የሚቀርበው የዘር፣ የምርምር ውጤቶች እና ተረፈ ምርት የሚከተሉትን መረጃ አካትቶ መያዝ አለበት፡-

ሀ) የሰብል ምርት ዓይነት፣ ዝርያ፣ ብዛት (በኩንታል)፣ የተመረተበት ዓመት፣

ለ) የእንሰሳት ዓይነት፣ የተወለደበት ቀን፣ ወር፣ ዓመት ምህረት፣ የዝርያ ዓይነት እና ብዛት በቁጥር፣

ሐ) የእንሰሳት ተዋጽኦ፣ ዓይነትና መጠን፣

መ) የእርሻ መሣሪያዎች ዓይነት፣ ብዛት በቁጥር፣ የተመረተበት ዓመት፣

ሠ) የዘርና ተረፈ ምርቱ የጥራትና የእርጥበት ደረጃ፣

ረ) የዘርና ተረፈ ምርት ገቢና ወጪ ሰነድ ቁጥርና ቀን እንዲሁም ሌሎች አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎች፡፡

## 5.2 የገበያ ጥናት እና መረጃ አያያዝ

5.2.1 የመንግሥት ዘር ኢንተርፕራይዞች የሁሉንም የዘር ክፍሎች ዋጋ በጋራ የሚወስኑት በየዓመቱ በሚካሄደው የዘር መድረክ ላይ የሚወሰነው የዘር ዋጋ እንደመነሻ ያገለግላል፤

5.2.2 የምርምር ውጤቶች እና ተረፈ ምርት ለሽያጭ ከመቅረቡ በፊት ወቅታዊ እና እንደየማዕከላቱ አካባቢ በገበያ ጥናት ዳሰሳ እንዲደገፍ ይደረጋል፤

5.2.3 የዘርና ተረፈ ምርት ሽያጭ የገበያ ጥናት እንደምርቱ አይነትና የጥራት ደረጃ የወቅቱንና የወደፊት ገበያው ምን ሊመስል እንደሚችል ይወሰናል፤

5.2.4 በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ በመታገዝ ተከታታይነት ባለው አጠቃላይ የሀገር ውስጥና የውጭ የገበያ ሁኔታን በተመለከተ መረጃ በማሰባሰብ፣ በመተንተንና በማጠናቀር የምርምር ውጤቶችና ተረፈ ምርት ሽያጭ ዋጋ ይወሰናል፤

5.2.5 የተቋሙን ጥቅም ለማስጠበቅ የገበያ መረጃዎች ለተገቢው (ለመረጃው ተጠቃሚና ሥራ ላይ ለሚያውለው) አካል ብቻ እንዲደርሱ ይደረጋል፤

5.2.6 ተፈላጊው የገበያ ጥናት መረጃ በወቅቱ ለውሳኔ ሰጭው አካል ቀርቦ ትክክለኛና ፈጣን ውሳኔ ለመስጠት እንዲያስችል ይደረጋል፤

## 5.3 የምርምር ውጤቶችና ተረፈ ምርት የሽያጭ ትውውቅ

የምርምር ውጤቱንና ተረፈ ምርቱን ዝርዝር መግለጫ ከምስል ጋር በተቋሙ ድህረ-ገጽ እንዲለጠፍ እንዲሁም በሌሎች ልዩ ልዩ የመረጃ ማሰራጫ መንገዶች እንዲተዋወቁ ይደረጋል።

## 5.4 የሽያጭ ስልቶች

የኢንስቲትዩቱ የምርምር ውጤቶችና ተረፈ ምርቶች ሽያጭ በሚከተሉት ስልቶች መሰረት ይከናወናል፤

5.4.1 በጨረታ

5.4.2 አስቀድሞ በሚገባ የውል ስምምነት

5.4.3 ከዚህ በላይ በተገለፁት የሽያጭ ስልቶች መሸጥ የማይቻልበት ሁኔታ ሲኖር ማዕከላት ዋጋ በመተመን በውስጥ ማስታወቂያ ሽያጭ ማከናወን ይችላሉ።

## 5.5 የዘር ዋጋ ትመና

5.5.1 የወቅቱን የመነሻ ዘር የማምረቻ ወጪ ትንተና ለእያንዳንዱ የዘር ደረጃ (አራቢ፣ ቅድመ መስራች እና መስራች) በመስራት የመሸጫ ዋጋ ይተመናል፤

5.5.2 ትመናውን መነሻ በመድረግ የማምረቻ ወጪ ላይ 15% በመጨመር ዋጋውን ተምኖ የሽያጭ ኮሚቴው ለማዕከላት ያሳውቃል፤

5.5.3 የማምረቻ ወጪ ትንተና ላልተሰራላቸው የምርት ዓይነቶች የተመሰከረለት ዘር ወቅታዊ የመሸጫ ዋጋን መነሻ በማድረግ በእያንዳንዱ የዘር ደረጃ ላይ ለአራቢ 20%፣ ለቅድመ መስራች 15% እና ለመስራች 10% በመጨመር የመሸጫ ዋጋ ይተመናል፡፡

## 5.6 የዘር ሽያጭ አፈጻጸም

5.6.1 የምርት ዘመኑ የዘር ብዜት ስራ ከመጀመሩ በፊት የዘር ማባዛት ፈቃድ ያላቸው አካላት (የምርጥ ዘር ድርጅቶች፣ የግል ዘር አምራቾች፣ ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት፣ የክልል ግብርና ምርምር ተቋማት) እንዲባዛላቸው የሚፈልጉትን የዘር መጠንና ዓይነት በደብዳቤ አቅርበው የመግባቢያ ሰነድ ከኢንስቲትዩቱ ጋር በግብርና ሚኒስቴር አማካኝነት እንዲፈራረሙ ይደረጋል፤

5.6.2 ኢንስቲትዩቱ በማዕከላት የተባዛው ዘር በተለያየ የዘር ደረጃ፣ ዝርያ እና የምርት መጠን ለዚሁ ሥራ በተዘጋጀው ድረ-መረብ መተግበሪያ ላይ መረጃውን በማስገባት ምርቱ ለሽያጭ ይቀርባል፤

5.6.3 ማንኛውም የዘር አምራችነት ፈቃድ ያለው የመነሻ ዘር ጠያቂ አካል የሚፈልገውን ዘር በሰብል አይነት፣ በዝርያ እና በመጠን በመግለጽ በድረ መረቡ አማካይነት ካሉበት ስፍራ ሆነው አገልግሎቱን ማግኘት እንዲችሉ ይደረጋል፤

5.6.4 ከተቋሙ ጋር ውል የተፈራረሙ አካላት የግዥ ጥያቄያቸውን ከድረ-መረቡ ላይ የድልድሉን ኮፒ በመያዝ ከማዕከላት ጋር ግብይቱ ይከናወናል፤

5.6.5 ውል ላልገቡ ዘር አምራቾች ከወረዳው ህጋዊ ደብዳቤ በመያዝ ለማዕከላት የዘር ጥያቄ በማቅረብ የስራ ዘርፉ በድረ-መረብ ላይ በማስገባት ዘሩ እንዲጠይቅላቸው ተደርጎ በተገኘው መጠን ሽያጭ ይከናወናል፤

5.6.6 የዘር ድልድሉ የተደረገላቸው ዘር ገዥዎች በተተመነው ዋጋ መሰረት ክፍያ መፈጸማቸው ሲረጋገጥ የገዙትን ዘር ከማዕከላት መጋዘኖች ይረከባሉ፤

5.6.7 ዘር ገዥዎች የገዙትን ዘር በውሉ ላይ በተቀመጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ የማንሳት ግዴታ አለባቸው፤

## 5.7 የእርሻ መሳሪያዎች ብዜትና ሽያጭ

5.7.1 ለሽያጭ የተዘጋጀው የእርሻ መሳሪያ በግብርና ምህንድስና ምርምር ዘርፍ ጥራቱ እንዲረጋገጥ ይደረጋል፤

5.7.2 ዓመታዊ የእርሻ መሳሪያዎች ብዜትና ሽያጭ ዕቅድ ለቴክኖሎጂ ተጠቃሚዎች የማስተዋወቅ ስራ የሚከናወንባቸው ወረዳዎች ዝርዝር ይዘጋጃል፤

5.7.3 የግብርና ምህንድስና ምርምር ስራ ዘርፍ በየጊዜው የሚያወጣቸውን ቴክኖሎጂዎች እንደ ገበያው ሁኔታ እያጠና የዋጋ ተመን በማዘጋጀት ለሚመለከተው ያሳውቃል፤

5.7.4 የተዋወቀውን የእርሻ መሳሪያ ለመግዛት ፍላጎት ያሳዩ ተጠቃሚዎች (አርሶ አደር፣ አርብቶ አደር፣ የግል ድርጅት ወይም ሌላ ፈቃድ የተሰጠው አካል) ከኢንስቲትዩቱ ጋር የሽያጭ ውል ስምምነት ይፈርማል፤

5.7.5 ተጠቃሚ የተፈረመውን ውል ስምምነት በመያዝ ለፋይናንስና ግዥ ሥራ አስፈፃሚ በማቅረብ ክፍያውን ፈጽሞ የእርሻ መሳሪያውን ከግብርና ምህንድስና ምርምር ዘርፍ ይረከባል፤

## 5.8 የእርሻ መሳሪያዎች ተረፈ ምርት ሽያጭ

5.8.1 በግብርና ምህንድስና ምርምር ዳይሬክቶሬት የተሰበሰቡና ግልጋሎት ሊሰጡ የማይችሉ የብረታ ብረት ቁርጥራጮችና አንዳንድ ብረቶች በተዘጋጀላቸው ማስቀመጫ ውስጥ እንዲቀመጡ ይደረጋል፤

5.8.2 የመሰረታዊ አገልግሎቶች ሥራ አስፈፃሚ በዓመት አንድ ጊዜ በሚቀርብለት የተረፈ ምርት የማስወገድ ጥያቄ መሰረት ወይንም ዓመታዊ የማዕከል ተረፈ ምርቶች ማስወገጃ ጊዜ በማዕከል ዳይሬክተር በሚሰየም የተረፈ ምርት አስወጋጅ ኮሚቴ አስተባባሪነት በመንግስት የንብረት አወጋገድ ደንብ መሰረት እንዲወገድ ለሚመለከተው አካል ጥያቄ ይቀርባል፣ ሲፈቀድም እንዲወገድ ይደረጋል፤

## 5.9 የእንስሳት ዘር ሽያጭ

5.9.1 ለሽያጭ የተዘጋጀው የእንስሳት ቴክኖሎጂ (ዓይነት፣ ዝርያ፣ ዘር፣ ጊደር፣ ኮርማ፣ ጫጩት) በእንስሳት ምርምር ዘርፍ ጥራቱ እንዲረጋገጥ ይደረጋል፤

5.9.2 ዓመታዊ የእንስሳት ቴክኖሎጂዎች ብዜትና ሽያጭ ዕቅድ ለቴክኖሎጂ ተጠቃሚዎች የማስተዋወቅ ስራ የሚከናወንባቸው ወረዳዎች ዝርዝር ይዘጋጃል፤

5.9.3 የእንስሳት ምርምር ዘርፍ በየጊዜው የሚያወጣቸውን ቴክኖሎጂዎች እንደ ገበያው ሁኔታ እያጠና የዋጋ ተመን በማዘጋጀት ለሚመለከተው ያሳውቃል፤

5.9.4 የእንስሳት ዘር ሽያጭን በተመለከተ በዋና መስሪያ ቤት በሚቋቋመው የዋጋ ትመና ኮሚቴ አማካይነት የወቅቱ የመሸጫ ዋጋ ይወሰናል፤

5.9.5 በዚህ መመሪያ የተቀመጡትን መሰረት በማድረግ ሽያጩ በማዕከላት የሚከናወን ይሆናል፡፡

## 5.10 የእንስሳት ተረፈ ምርት ሽያጭ

5.10.1 ለምርምር አገልግሎት የማይውሉ እንስሳት ወይም የእንስሳት ተዋጽኦዎች ዝርዝር መግለጫ (በአይነት፣ በብዛት) በዘርፉ ተለይቶ ለሽያጭ እንዲቀርቡ ይደረጋል፤

5.10.2 ከላይ በቁጥር 5.10.1 የተገለፁት በማዕከሉ የሽያጭ ኮሚቴ የዋጋ ትመና ተሰርቶ ሽያጩ ይፈፀማል፡፡

## 5.11 የችግኝና ቁርጥራጭ ብዜት ሽያጭ

5.11.1 ለሽያጭ የተዘጋጀው ችግኝና ቁርጥራጭ (ዓይነት፣ ዝርያ፣ መጠን) በሚመለከተው የምርምር ዘርፍ ጥራቱ እንዲረጋገጥ ይደረጋል፤

5.11.2 ዓመታዊ የችግኝና ቁርጥራጭ ብዜትና ሽያጭ ዕቅድ ለቴክኖሎጂ ተጠቃሚዎች የማስተዋወቅ ስራ የሚከናወንባቸው ወረዳዎች ዝርዝር ይዘጋጃል፤

5.11.3 የሚመለከተው የምርምር ዘርፍ በየጊዜው የችግኝና ቁርጥራጭ ገበያ ሁኔታውን እያጠና የዋጋ ተመን በማዘጋጀት ለሚመለከተው ያሳውቃል፤

5.11.4 የችግኝና ቁርጥራጭ ሽያጭን በተመለከተ በዋና መስሪያ ቤት በሚቋቋመው የዋጋ ትመና ኮሚቴ አማካይነት የወቅቱ የመሸጫ ዋጋ ይወሰናል፤

5.11.5 በዚህ መመሪያ የተቀመጡትን መሰረት በማድረግ ሽያጩ በማዕከላት የሚከናወን ይሆናል፣ ሪፖርቱም ለኢንስቲትዩቱ ይቀርባል፡፡

## 6. ሌሎች ልዩ ልዩ ተረፈ ምርቶች ሽያጭ

6.1 ኢንስቲትዩቱ በሥሩ ባሉ ማዕከላት ውስጥ ያመረተውን የተፈጥሮ ሃብት ምርቶች እንዲሁም ሌሎች፣ ከዘር የተረፉ ለምግብነት የሚውሉና የማይውሉ ሰብሎች ብጣሪ፣ ቋሚ የደን ተክሎች በማዕከሉ የሽያጭ ኮሚቴ የገበያ ጥናት ተደርጎ በሚቀርበው የውሳኔ ሃሳብ መሰረት ዋጋ ከተወሰነ በኋላ እንዲሸጡ ይደረጋል፣ ሪፖርቱም ለኢንስቲትዩቱ ይቀርባል፡፡

6.2 ከዚህ በላይ በተቀመጠው የሽያጭ ሂደት መነሳት ያልቻለ ምርት መሆኑ ሲረጋገጥ እና ሽያጩ በሌላ አካል ላይ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ጉልህ ተፅዕኖ የማያደርስ እንዲሁም በህግ ክልከላ የተደረገበት ካልሆነ በዋና ዳይሬክተር /በምክትል ዋና ዳይሬክተር/ በማዕከል ዳይሬክተር ውሳኔ የምርት ሽያጩ ይከናወናል፤

6.3 የምርምር ውጤቱና ተረፈ ምርቱ ለተለያዩ ተባዮች፣ ለድንገተኛ አደጋ የተጋለጠ ከሆነ፣ በማሽን የተጎዱ እና በቀላሉ ሊበላሹ የሚችሉ ከሆነ በሌላ ዘዴ የምርቱን ደህንነት ለማስጠበቅ አዳጋች መሆኑ ከተረጋገጠ ለኢንስቲትዩቱ የበላይ ኃላፊ/ ለማዕከል ዳይሬክተር/ ለውሳኔ ይቀርባል፡፡

## 7. የሽያጭ ኮሚቴ አሰያየም

7.1 ሽያጩን በየጊዜው እያጠና ገምግሞ የውሳኔ ሃሳብ የሚያቀርብ ተጠሪነቱ ለዋና ዳይሬክተር/ ምክትል ዋና ዳይሬክተር/ ማዕከል ዳይሬክተር የሆነ አምስት አባላት ያሉት የሽያጭ ኮሚቴ በዋና መስሪያ ቤትና በማዕከላት ይቋቋማል፤

7.2 የሽያጭ ኮሚቴው አባላት ከመነሻ ቴክኖሎጂ ብዜትና ዘር ምርምር፣ ከግብርና ኤክስቴንሽን ምርምር፣ ከምርምር ጥራት ማረጋገጫና ግምገማ፣ ከመሰረታዊ አገልግሎቶች ሥራ አስፈፃሚ፣ ከፋይናንስና ግዥ ሥራ አስፈፃሚ የተውጣጡ ይሆናል፤

7.3 የኮሚቴው ሰብሳቢ የመነሻ ቴክኖሎጂ ብዜትና ዘር ምርምር ሲሆን የሽያጭ ኮሚቴው ፀሐፊ ደግሞ የግዥ ባለሙያ ይሆናል፡፡

7.4 የግብርና ኢኮኖሚክስ ምርምር ለሽያጭ ኮሚቴው የገበያ ጥናት በማድረግ ድጋፍ ያደርጋል፡፡

## 8. የሽያጭ ኮሚቴ ተግባርና ኃላፊነት

8.1 የዘር፣ ሌሎች የምርምር ውጤቶች እና ተረፈ ምርት ሽያጭ ኮሚቴ ሥራውን የሚያከናውነው የመንግሥት የግዥና ንብረት ማስወገድ አዋጅ፣ ደንብና መመሪያዎች እንዲሁም በዚህ መመሪያ መሰረት ይሆናል፤

8.2 የሽያጭ ኮሚቴው አባላት በጨረታ ሰነዱ ላይ በግልጽ ከሰፈሩት መብትና ግዴታዎች እንዲሁም ከዚህ የዘር፣ የምርምር ውጤቶችና ተረፈ ምርት ሽያጭ መመሪያ ውጪ ፈጽመው ከተገኙ ተጠያቂነት አለባቸው፤

8.3 በወጣው ጨረታ ላይ ከሚሳተፉ ተጫራቾች ውስጥ ዝምድና ያለው ወይም የባለቤትነት ድርሻ ወይም የጥቅም ተጋሪ የሆነ የኮሚቴ አባል መኖሩ ከተረጋገጠ በጨረታው ሂደት እንዳይሳተፍ ይደረጋል፡፡

8.4 ማንኛውም የሽያጭ ኮሚቴ አባል የሥነ-ምግባር መርሆዎችን የማክበር ግዴታ አለበት፡፡

## 9. የሽያጭ ውል

9.1 በጨረታው አሸናፊ ከሆነ ተጫራች ጋር ኢንስቲትዩቱ የሽያጭ ውል (ቅፅ - 3) መሰረት መፈፀም አለባቸው፡፡

9.2 በማንኛውም የምርት ሽያጭ ውል ወቅት የምርቱ ናሙና በሻጭና በገዥ በፖስታ ታሽጉ አባሪ ሆኖ ይቀመጣል፡፡

10. **ዋስትና** አሸናፊ ተጫራቾች ለውል አፈፃፀም ማስከበሪያ ያሸነፉበትን ጠቅላላ ዋጋ በባንክ በተረጋገጠ የገንዘብ መክፈያ ማዘዣ የጠቅላላ ዋጋውን 10 በመቶ ዋስትና እንዲያስይዝ ይደረጋል፡፡

11. **የእርምጃ አወሳሰድ** የዘር፣ የሌሎች የምርምር ውጤቶችና ተረፈ ምርት ሽያጭ ጨረታ አሸናፊ የሆነው ተጫራች ከኢንስቲትዩቱ ጋር በሚገባው የሽያጭ ውል ስምምነት መሠረት ካልፈጸመ ኢንስቲትዩቱ አግባብነት ባላቸው ሕጎች መሰረት ተገቢውን እርምጃ ይወስድበታል፡፡

## 12. ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

12.1 ኢንስቲትዩቱ የግብርና ሚኒስቴር ከሁሉም የክልል ግብርና ቢሮዎች፣ ከምርጥ ዘር ድርጅቶች እና ከዘር አባዦች አሰባስቦ በሚልክለት የዘር ፍላጎት መሰረት በዘር ደረጃና በዝርያ ዓይነት አሰባስቦ ያስቀምጣል፤

12.2 የደንበኞች ቅሬታ እንዲሁም ግብረ-መልስ (Feed Back) መቀበያ ዘዴዎች ጥቅም ላይ እንዲውሉ ይደረጋል፡፡

12.3 ማዕከላት የተመረተው የዘር መጠን በምርት ዘመኑ ተሸጦ ከመጋዘን እንዲነሳ ያደርጋሉ፡፡

## 13. የተሻሩ መመሪያዎች

ከዚህ በፊት በስራ ላይ የነበረው የኢንስቲትዩቱ የተረፈ ምርት ሽያጭ መመሪያ እንዲሁም በተለያዩ ጊዜያት ዘርና ተረፈ ምርት ሽያጭን አስመልክቶ የወጡ መመሪያዎችና ሰርኩላሮች በዚህ መመሪያ መሰረት ተሽረዋል፡፡

## 14. መመሪያውን ስለማሻሻል

ኢንስቲትዩቱ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው አፈፃፀሙን በመገምገም በማናቸውም ጊዜ መመሪያውን ሊያሻሽለው ይችላል፡፡

## 15. መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ በኢንስቲትዩቱ ዋና ዳይሬክተር ከተፈረመበት ከ............ ቀን 2016 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

---------------- ዋና ዳይሬክተር የኢትዮጵያ ግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት

# አባሪ፡ ልዩ ልዩ ቅፆች

## የኢትዮጵያ የግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት የዘር

## ምርት ማሳወቂያ ቅፅ

ቀን ______________________________

ማዕከል _________________________ ዘሩ የተመረተበት ዓመት _________________________ ቅፅ - 1

| የቴክኖሎጂው ዓይነት | የተባዛው ዝርያ ዓይነት | መለኪያ | የተገኘ ምርት መጠን (ኩ/ል) (ሀ) | | | ለቀጣይ ዘር ብዜት የሚውል የዘር መጠን (ኩ/ል) (ለ) | | | ለቴክኖሎጂ ቅድመ-ማስተዋወቅ የሚውል ዘር መጠን (ኩ/ል) (ሐ) | | | ለተጠቃሚዎች ሊሰራጭ የሚችል መጠን (ኩ/ል) (መ = ሀ - (ለ + ሐ) | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | አራቢ. | ቅድመ መስራች | መስራች | አራቢ. | ቅድመ መስራች | መስራች | አራቢ. | ቅድመ መስራች | መስራች | አራቢ. | ቅድመ መስራች | መስራች |
| ጤፍ | ቁንጮ | | | | | | | | | | | | | |
| | ቦሰት | | | | | | | | | | | | | |
| | ፀደይ | | | | | | | | | | | | | |
| | ኮራ | | | | | | | | | | | | | |
| | ድምር | | | | | | | | | | | | | |
| ስንዴ | | | | | | | | | | | | | | |

| | | | | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | | | | |
| | ድምር | | | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | | | | |
| | ድምር | | | | | | | | | | | | | |

ያዘጋጀው፡ ስም______________________________________ ፊርማ______________________________________

ያረጋገጠው፡ ስም_____________________________________ ፊርማ _____________________________________

**የኢትዮጵያ የግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት የምርምር**

**ምርት/ ተረፈ ምርት ገቢ ማድረጊያ ቅፅ**

ቀን ______________________________

ማዕከል ______________________________

የምርምር ክፍል ______________________________

ቅፅ - 2

| ተራ ቁጥር | የቴክኖሎጂ ዓይነት | ዝርያ | የዘር ደረጃ | መለኪያ | ብዛት | አስተያየት |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | |
| | | | | | | |
| | | | | | | |
| | | | | | | |
| | | | | | | |
| ድምር | | | | | | |

ያዘጋጀው፡ ስም_____________________________________ ፊርማ_____________________________________

ያረጋገጠው፡ ስም_____________________________________ ፊርማ _____________________________________

ቅፅ - 3

**የኢትዮጵያ የግብርና ምርምር**

**ኢንስቲትዩት የተረፈ ምርት ሽያጭ**

**ውል ቅፅ**

ይህ የተረፈ ምርት ሽያጭ ውል ከዚህ በኋላ ሻጭ በሚባለው በ ___________________________ ምርምር ማዕከል አድራሻ ______________________________ ከተማ ____________________ እና ከዚህ በኋላ ገዥ በሚባለው በ ______________________ አድራሻ ______________________________ ከተማ ______________________________ መካከል የተደረገ የውል ስምምነት ነው፡፡

1) የውሉ ዓላማ፤

ሻጭ የምርምር ሥራ የሚያከናውን የፌደራል መንግስት መ/ቤት ሲሆን ከምርምር ሥራ የተረፉትን የምርምር ተረፈ ምርቶችን ለመሸጥ ባወጣው ጨረታ መሰረት ገዥ ተወዳድሮ በማሸነፉ በጠቅላላው _________________ ኩንታል ተረፈ ምርትን በ _________________ ብር ለመግዛት የተደረገ የሽያጭ ውል ነው፡፡

2) የሻጭ ግዴታ፤

2.1 በሽያጭ ማስታወቂያው ላይ የተዘረዘሩትን ተረፈ ምርቶች ለገዥ ማስረከብ ይኖርበታል፡፡

2.2 ገዥ የገዛቸውን ተረፈ ምርቶች በወቅቱ እንዲያነሳ ምቹ ሁኔታ መፍጠር ይኖርበታል፡፡

3) የገዥ ግዴታ፤

3.1 ለመግዛት የተስማማበትን የተረፈ ምርት ዋጋ ሙሉ በሙሉ በሻጭ የባንክ ሂሳብ ቁጥር በቅድሚያ ገቢ ማድረግ ይኖርበታል፡፡

3.2 የገዛውን ተረፈ ምርት በ ____________________ ቀናት ውስጥ ምርቱን ማንሳት ይኖርበታል፡፡

3.3 በተራ ቁጥር 3.2 መሰረት ምርቱን ባያነሳ በእያንዳንዱ ቀን በገዛው መጠን ብር ______________________________ የሚከፍል ይሆናል፡፡

4) የውሉ አካሎች፤ አጠቃላይ የውል ሁኔታዎች፤ የሻጭ የጨረታ ማስታወቂያ፤

የጨረታ ማስከበሪያ ሰነድ እና የገዥ የዋጋ ማቅረቢያ፤ ሻጭ

ለገዥ ጨረታውን ማሸነፉን ያስታወቀበት ሰነድ፤

5) አለመግባባቶች የሚፈቱበት ሥርዓት፤

በገዥና ሻጭ መካከል አለመግባባት ቢፈጠር ሁለቱም ወገኖች ጉዳዩን በጋራ ድርድር መፍታት አለባቸው፤

በጋራ ውይይት/ድርድር/ መፍታት ካልቻሉ ጉዳዩ በፍርድ ቤት ይታያል፡፡

6) የህጎች ተፈፃሚነት፤

በዚህ ውል ውስጥ የተጠቀሱት ስምምነቶች ግዴታዎች እንዲሁም በሥራ ላይ ያሉት የሃገሪቱ የውል ህግ ድንጋጌዎች በዚህ የሽያጭ ውልም ላይ ተፈፃሚ ይሆናሉ፡፡

አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ተቋሙ/ማዕከሉ ያደረገውን ውል እንደውሉ አግባብ ከገዥ ጋር በመስማማት ማሻሻል ይችላል፡፡ ቅጽ-3

7) ውሉ የሚፀናበት ጊዜ፤

ይህ የሽያጭ ውል በገዥና ሻጭ መካከል ከተፈረመበት ከዛሬ ______________________ ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

ስለ ሻጭ፤

ስም __________________ ፊርማ _____________ ቀን_______________

ስለ

ገዥ፤

ስም

______

______

_____

ፊርማ

______

______

**ቀን____**

______

____

**<u>በውሉ ሲፈረም የነበሩ እማኞች፤</u>**

| | ስም | ፊርማ | ቀን |
|---|---|---|---|
| 1) | ______________________ | _______________ | _______________ |
| 2) | ______________________ | _______________ | _______________ |
| 3) | ______________________ | _______________ | _______________ |

**የኢትዮጵያ የግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት**

**የተሸጠ የዘር/ ተረፈ ምርት የበር**

**መውጫ ቅፅ**

**ቅፅ** -

4

ቀን ______________________________

ለጥበቃ ሥራ ክፍል ከመሰረታዊ

አገልግሎቶች ሥራ አስፈፃሚ

ከዚህ በታች በቀረበው ዝርዝር መሰረት ንብረቱን አቶ/ወ/ሮ/ወ/ሪት ______________________________ ከግቢ ይዘው እንዲወጡ ተፈቅዷል፡፡

| ተራ ቁጥር | የዘር/ተረፈ ምርት ዓይነት | መለኪያ | ብዛት | የወጪ ሰነድ ቁጥር |
|---|---|---|---|---|
| | | | | |
| | | | | |
| | | | | |
| | | | | |
| | | | | |
| ድምር | | | | |

የፈቀደው ኃላፊ _____________________ ፊርማ ____________________

Ethiopian Institute of Agricultural Research (EIAR)
Melkassa Agricultural Research Center (MARC) Agricultural
Engineering Research technologies USE AGREEMENT

One of the objectives of ______project is to test site specific small scale mechanization in Ethiopia by availing new research and develop equipment for various interventions. These implements or equipment will be used to test and promote technologies in the project areas and eventually beyond. Therefore, EIAR as a __ project implementer need to enter into an agreement with a user that is entirely dedicated for the project purpose.

This document will serve as an agreement between the EIAR and ____________________ (User) about the temporary /permanent/ handover of technology for use over the next ________________ years or beyond. The project will allow for the use of this item free of charge for the aforementioned length of time and at the end of the project EIAR together with ________________ project will decide on the extension and use of the equipment.

EIAR will:

Select and award users of the technology/equipment with Ethiopian Institute of Agricultural Research (EIAR).
Give the required technical and business trainings (at least the basic operational and maintenance techniques for the technologies).

Develop the data collection format & obtain information in a timely manner.

Collect the technology/equipment after the agreed period or will decide better alternatives to the best of the project.

Not be liable in any sort of accidents that may be occurring during the use of the equipment.

The user will:

Use the equipment for the intended purpose only.

Operate the equipment in the appropriate location.

Conduct any required maintenance and repair at his/her own cost.

Support _______________ project knowledge management events (such as visits, demonstrations, field days etc.) arranged by EIAR and other collaborators especially project implementing partners (names of the partners…..) for the popularization and demonstration of agricultural technologies and Natural Resources for knowledge sharing.

Provide all the required data in a timely manner and as per the format provided.

Inform EIAR, and project implementing partners and other relevant government office (Police) of any new/unexpected events such as damage or theft on/to the equipment.

Provide service to the community at a reasonable price if the technology is intended for commercial demonstration and public use.

Return back the equipment after the agreed period.

Use of the technology/equipment:

The user shall be responsible for using the equipment with expertise and carefully for the purpose for which it is intended.
The technology/equipment, at all times, remains the property of EIAR for the duration of this agreement and beyond. The user cannot sell, pledge or transfer the technology/equipment to any other party.

In return, the ________________ project expects data on the usage of this implement and any other information as required will be provided to project staff using formats developed by the project.

USER

On behalf of Ethiopian Institute of Agricultural Research (EIAR)

Agricultural Engineering Research Process

Signature__________________ Date_________________

Signature_________________ Date___________________

Witness up on the signature of the agreement (Name & Signature)

Name ____________________________ Signature ____________________

Name ____________________________ ____________________ Signature

____________________

Name ____________________________ Signature

This agreement will be into effect starting from the date of signature by both parties. It should also bear the official stamp of the institute or the center.

**ቀን፡- -------------------------------**

**የኢትዮጵያ የግብርና ምርምር**

**ኢንስቲትዩት የመልካሳ ግብርና ምርምር ማዕከል**

**የግብርና ምህንድስና ምርምር ዳይሬክቶሬት/የስራ ሂደት**

**<u>የተሻሻሉና ውጤታማ የግብርና ቴክኖሎጂዎች ስርጭትና አጠቃቀም ትግበራ ሥራ ውል</u>**

**ውል ሰጪ፡- የግብርና ምህንድስና ምርምር የስራ ሂደት <u>መልካሣ</u>**

**ውል ተቀባይ ስም፡- ------------------------------------------------------**

**ስራ፡- ---------------------------------------------------------------------- ስልክ**

**ቁጥር፡- ------------------------------------------------------------- አድራሻ**

**ክልል፡- ----------------------------------------------------------- ዞን፡- -------**

**--------------------------------------------------------------- ወረዳ፡- ------------**

**------------------------------------------------------ ቀበሌ፡- --------------------**

**-----------------------------------------------**

**የቴክኖሎጂው ስም____________________________________**

**የቴክኖሎጂው ዓይነት ፡- ------------------------------------------------------------------------**
**----------የቴክኖሎጂው ተግባር __________________________________________________**

የቴክኖሎጂው የስርጭት ባህሪ 1) በጊዜያዊነት ለ ---------------- ዓመት/ታት

2) በቋሚነት የውል

ተቀባይ ግዴታ፡-

ከማዕከሉ የተሻለና ውጤታማ የግብርና ቴክኖሎጂ በተሰጠኝ ሥልጠና መሠረት ተጠቅሜ ለበለጠ ውጤት አስፈላጊውን መረጃ በትክክል ለመስጠት ፣ ጠቃሚነቱንም የራሴን ቤተሰብና ሌሎች ተጠቃሚዎችን ከአምስት በላይ ለሆኑት አጎራባች አርሶ/አርብቶ አደሮች ስለተረከብኩት ቴክኖሎጂ ዕውቀቴን አካፍዬ የበለጠ ውጤት ለማምጣት ቃል የገባሁ ሲሆን የተረከብኩትን ቴክኖሎጂ የኢትዮጵያ የግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት የግብርና ምህንድስና ምርምር የሰጠኝን ቴክኖሎጂ ከታለመለት ዓላማ ውጪ ላልጠቀምና ለሌላ አርሶ/አርብቶ አደር በሽያጭም ሆነ ከኢንስቲትዩቱ ዕውቅናና ከተሰጠኝ ፈቃድ ውጪ ላላስተላልፍ ግዴታ እንዳለብኝ አውቄ ይህንንም በፊርማዬ አረጋግጣለሁ። ይህንን ሳልተገብር ብቀር በህግ የምጠየቅ መሆኑን የተቀበልኩ መሆኑን አረጋግጣለሁ።

ስም፡- ------------------------------------ ፊርማ፡- ---------------------- ቀን፡- -------------------

## መልካሳ ግብርና ምርምር ማዕከል

## የግብርና ምህንድስና ምርምር የስራሂደት

## በውል ስምምነት ተዘጋጅቶ ለሙያዊ ክንውንና ክትትል ተያያዥ አቅርቦትና የእጅ ዋጋ መቆጣጠሪያና መክፈያ ቅፅ

**ውል**

እኔ ---------------------------------------- የ -------------------------------------- ስራ ልዩ ሙያተኛ የሆንኩ በመልካሳ ግብርና ምርምር ማዕከል የ ---------------------------------------- ምርምር የሥራ ሂደት ለሚያሰራው የ --------------------------------------------------------------- ------------------------ ከዚህ በታች በተዘረዘሩት በሰራኂቸው ቀናት አንፃር የተጠቀሱትና ሙያዊ ስራዎች ለመስራት ከማዕከሉ ጋር ውለታ ገብቻለሁ፡፡

| ተ. ቁ | ቀን | ሙያዊ ስራዎች የተሰራበት አካል ፣ ቦታ እና መሳሪያ | ከኔ የቀረበ አቅርቦት | የዕለቱ የተጠራ ዋጋ | ስም | ፊርማ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | | | | | | |
| | | | | | | |
| 2 | | | | | | |
| | | | | | | |
| 3 | | | | | | |
| | | | | | | |
| 4 | | | | | | |
| | | | | | | |
| 5 | | | | | | |
| | | | | | | |

በ --------------------- ቀን ---------------- ዓ.ም በድርድር ውል መሠረት የ------------- ቀን የሙያ ዋጋ ---------------- የአንድ ቀን የሙያ ዋጋ ------------------------------------------------ -- የ --------------------- ቀናት ዋጋ ብር ------------------------- የአንዱ ------------------------ ነጠላ ዋጋ ------------------------------ የ -------------------------- ዋጋ ብር ---------------------- ከእኔ -------------------------- አቅርቦት ዋጋ ------------------------------ የ ----------------------- -------- ዋጋ ብር ----------------------- በድምሩ ብር ------------------- (--------------------------- ---------------------------------------------------) በ ------------ ቀናት በጥራትና በተፈለገው ዓይነት ስራውን አጠናቅቄ ለማስረከብና በእኔ አሰራር ከውሉ ቢጎድል በራሴ ኪሣራ አስተካክዬ ለመስራት ተስማምቻለሁ፡፡

**ውል ሰጪውም በውሉ መሠረት ሥራው ሲጠናቀቅ ክፍያው ለመፈፀም ውለታ ሰጥቷል፡፡**

**<u>ውል ሰጪ ውል ተቀባይ</u>**

**ስም ------------------------------ ፊርማ ---------- ቀን------------- ስም ---------------------- ፊርማ -------------- ቀን ---------------**

**መልካሣ ግብርና ምርምር ማዕከል አስተያየት ---------------------------------------------------- ------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------- ------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------- --------------------------------------------------------**